# በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የተዘጋጀ
# የአገር ውስጥ ውሃ ትራንስፖርት የደህንነት እና ቁጥጥር መመሪያ

ቁጥር ------/2016

አዲስ አበባ

**(ረቂቅ)**

## ማውጫ


ክፍል አንድ....4
ጠቅላላ ድንጋጌ....4
1. መ ግ ቢ ያ....4
2. ትርጉም....5
3. የመመሪያው ዓላማ....6
4. የተፈፃሚነት ወሰን....7
5. የሀገር ውስጥ ውሃ መንገዶች ምደባ....7
6. በኢትዮጵያ የሀገር ውስጥ ውሃ መንገድ ገደብ....7
ክፍል ሁለት....8
7. የ ሀ መ ር ማ ስ መ ዝ ገ ብ ግ ዴ ታ....8
8. ለምዝገባ የሚቀርብ ማመልከቻ....8
9. በሐመሩ ላይ ምልክት ስለማድረግ....9
10. የጉዞ ብቁነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት....9
11. ምርመራና ፍተሻ....10
12. የሕይወት አድን ጥንቃቄዎች እና መሣሪያዎች....12
13. ከሐመር ስለሚወጣ ቆሻሻ....13
ክፍል ሦሥት....13
ሥልጠና እና የሐመር ሰራተኞች ብቃት....13
14. የሐመር ላይ ሰራተኞች ብቃት....13
15. ስልጠና እና ልምድ....15
16. የደህንነት ሥልጠና....16
ክፍል አራት....17
17. ተሳፋሪዎች እና ጭነትን ስለማጓጓዝ....17
18. ከፍተኛ የተሳፋሪዎች ቁጥር....17
19. እቃዎችን በብትን እና አደገኛ እቃዎችን ስለማጓጓዝ....18
20. በአደጋ ጊዜ ግዴታዎች እና ሪፖርት ማድረግ....18
21. የአደጋ ምርመራ ማድረግ....19
ክፍል አምስት....19
22. ችሎታ የማረጋገጫ መመዘኛ መስፈርቶች....20
23. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ....22
24. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት....24

25. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዕድሳት....24
26. ፍቃድ መሰረዝ....24
ክፍል ስድስት....24
27. አስተዳደራዊ እርምጃ....25
28. የሀገር ውስጥ ውሀ ወደብ ሀላፊነት እና ተግባር....26
29. የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለስልጣን ሀላፊነት ተግባር....27
30. የሚኒስቴሩ ተግባር እና ኃላፊነት....27
31. የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥራዓት....28
32. የሽግግር ወቅት....29
33. መመሪያ ስለማሻሻል....29
34. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ....29

# ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. መ ግ ቢ ያ

ኢትዮጵያ የብዙ ሐይቆችና ወንዞች ባለቤት ብትሆንም ለአገር ውስጥ የውሃ ትራንስፖርት አገልግሎት የዋሉት ጥቂቶች ናቸው። በአገልግሎት ላይ የዋሉትም ቢሆን አገልግሎቱን የሚሰጡ ሐመሮች ደህንነታቸው ተጠብቆ ዘላቂና አስተማማኝ አገልግሎት መስጠት የሚያስችላቸው የደህንነት ደረጃ መቆጣጠሪያ መስፈርት የላቸውም።

በአገልግሎት ዘርፉ የሚሰማሩ ሐመሮችን የደህንነት ደረጃ የማውጣትና ተግባራዊነቱን የመቆጣጠር ኃላፊነት በአዋጅ ቁጥር 549/1999 ለኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን በመሰጠቱ ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችለውን አቅጣጫ ለመከተል የዳሰሳ ምልከታዎችን ሲያደርግ ቆይቷል። በዚህ መሠረት በጅምር ደረጃ በመስኩ የተሰማሩ አገልግሎት ሰጪዎች አገልግሎት አሰጣጣቸው ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የዓለም አቀፍ አሰራሮችን ተሞክሮ መነሻ በማድረግ የገመገመ ሲሆን በቀጣይ የአገልግሎት አሰጣጡ እንዲዳብርና በዘርፉ ተገቢውን የውሃ ላይ ትራንስፖርት አገልግሎት የመስጠት አቅም እንዲኖረው ለማስቻል የደህንነት መመሪያ ረቂቅ አዘጋጅቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎበት መመሪያውን በሚመለከተው አካል ለማስጸደቅ እየተሰራ ይገኛል።

ቀደም ሲል በተካሄደው የዳሰሳ ምልከታዎች የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ያሉት ውሃዎች የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ካላቸው አቅም አንጻር ዘርፉን ለማሳደግ ያለው ዕድል ከፍትኛ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል።

በመሆኑም አጠቃላይ በሀገሪቱ ሐይቆችና ወንዞች ለምተው ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ከማመቻቸት ጎን ለጎን አሁን ያለውን ዝቅተኛ ወይም መጠነኛ የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ለማሳደግ፣ ደረጃውን የጠበቀና ቀጣይነት ያለው አገልግሎት መስጠት እንዲቻል በሀገር ውስጥ የውሃ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰማሩ ሐመሮች ምዝገባና ደህንነት ለመቆጣጠር፣ ሐመር በማስመጣት፣ በማምረት፣ በማደስ እና ሐመርን በማንቀሳቀስ ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላትን ለመቆጣጠር ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል።

ይህ መመሪያ የሀገር ውስጥ ውሃ ትራንስፖርት ደህንነት እና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር -----/2016 ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

## 2. ትርጉም

2.1. **ደህንነት**፡- ማለት የሐመሮች የውሃ ላይ ጉዞ ብቃት (ሴፍቲ) ማለት ነው፡፡

2.2. **ዴክ**፡- ማለት የሀመር ወለል ማለት ነው፡፡

2.3. **ዴክ አልባ** ማለት፡- ሐመር የወለል ሽፋን ወይም ጣሪያ የሌላት ሐመር ማለት ነው፡፡

2.4. **ባለዴክ ሐመር**፡- ማለት ከላይ ወለል (ጣሪያ) ያላት ማለት ሲሆን እንደሐመርዋ መጠን ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ወለሎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

2.5. **የሐመር አዘዥ**፡- ማለት ሐመርዋን ከቦታ ቦታ የማንቀሳቀስ ኃላፊነት ያለበት ሰው ማለት ሲሆን አጠቃላይ የሐመርዋ ኃላፊ ነው፡፡

2.6. **ሞገድ**፡- የውሃ የውስጥ ንቅናቄ ማለት ነው፡፡

2.7. **ድርጅት**፡- ማለት ሐመር በማንቀሳቀስ፣በማምረት፣ በመጠገን፣ በመግዛት እና መሸጥ ወይም ተመሳሳይ ስራ ላይ የተሰማሩ የግል ንግድ ወይም የንግድ ማህበር የሆነ ተቋም ነው፡፡

2.8. **የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት**፡- ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት የሚጠየቁ የትምህርት ደረጃን፣ የሰው ኃይል፣ የቢሮ አገልግሎት እና የኢንዱስትሪ መሳሪያን ላሟላ ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፡፡

2.9. **የንግድ ሥራ ፈቃድ**፡- ማለት ሐመር በማምረት፣ በመጠገን፣ በማደስ ወይም በሐመር የውሃ ትራንስፖርት ስራ ላይ ለመሥራት ከሚመለከተው የሚኒስቴር መ/ቤት የሚሰጥ ፈቃድ ማለት ነው፡፡

2.10. **ሐመር**፡- ማለት በሀገር ውስጥ ውሃ ላይ የሚንሳፈፍና ለትራንስፖርት ሥራ የሚውል የመጓጓዣ ዓይነት ሲሆን በተገጠመለት ውስጥ ሞተር /inboard engine/ ወይንም በውጫዊ አካሉ በተገጠመ ሞተር /outboard engine/ አማካኝነት የውሃ ላይ ጉዞ ለማድረግ የሚያስችል የባለሞተር ሐመር ዓይነት እና የመዝናኛ፣ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰሩ እንዲሁም በእጅ የሚቀዘፉ ሞተር አልባ ሐመሮችን ያካትታል፡፡

2.11. የሐመር አስመጪ፡- ማለት የንግድ ምዝገባ ፈጽሞ የባለሞተር ሐመሮችን በማስመጣት ስራ ላይ ለመሰማራት በዚህ የአሰራር ሥርዓት ውስጥ የተዘረዘሩትን መሥፈርቶች በማሟላት በሚመለከተው በባለስልጣን

መ/ቤት ብቃቱ ተረጋግጦ የብቃት ማረጋገጫ የሚያገኝ ድርጅት ወይም የንግድ ማህበር ነው፡፡

2.12. **የማሪታይም ዘርፍ አማካሪ** /Marine Consultant/:-ማለት በማሪታይም ዘርፍ በቴክኒካል ወይም በኦፕሬሽናል ወይም በሁለቱም የተዘረዘሩትን መሥፈርቶች በማሟላት በዘርፉ ለመሰማራት ብቃቱ በባለስልጣን መ/ቤቱ የተረጋገጠ ግለሰብ፣ ድርጅት ወይም የንግድ ማህበር ነው፡፡

2.13. **ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር**፡- ማለት የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

2.14. **ባለሥልጣን**፡- ማለት በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 መሠረት የተቋቋመው እና ስሙ የተሻሻለው የኢትዮጵያ የማሪታይም ባለሥልጣን ነው፡፡

2.15. **የሀመር አምራች**፡- የሀመር ግንባታ ላይ የተሰማራ ግለሰብ ወይም ድርጅት ማለት ነው፡፡

2.16. **የሀመር ጠጋኝ**፡- የሀመር ጥገና ስራ ላይ የተሰማራ ግለሰብ ወይም ድርጅት ማለት ነው፡፡

2.17. **የሀገር ውስጥ ውሃ ወደብ**፡- በወንዝ፣ ሀይቅ ወይም ግድብ ዳርቻ የተገነባ እና ለሀመር መጠጊያ የሚያገለግል እና የተለያዩ የውሃ ትራንስፖርት ስራዎች የሚከናወኑበት ስፍራ ነው፡፡

2.18. **የሀመር ሬጂስትራር**፡-ማለት ሀመሮችን የሚመዘግብ፣ የሚሰርዝ እና መረጃ አደራጅቶ የመያዝ ሀላፊነት የተሰጠው ማለት ነው፡፡

2.19. **ሰው**፡- ማለት የተፈጥሮ ወይም ህጋዊ ሰዉነት ያለው ማለት ነው፡፡

2.20. ጾታ አጠቃቀም በአንዱ ጾታ የተገለጸ ስም ለሌላኛው ጾታ ያገለግላል፡፡

## 3. የመመሪያው ዓላማ

መመሪያው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

3.1. በሐመሮች ላይ የሚሰሩ ሰራተኞች ተሳፋሪዎች የቱሪስቶች ሕይወትና ንብረት ዋስትናን ለማጋገጥ እንዲቻል፣

3.2. የዘርፉን የአገልግሎት አሰጣጥ ብቃት ለማሳደግ ዓለም አቀፍ አሰራሮችን በመከተል ለአካባቢው ነዋሪ እና ለጎብኚዎች አስተማማኝ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠትና ከመስኩም የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማሳደግ እንዲቻል፣

3.3. ሐይቆችና ወንዞችን ከብክለት በመከላከል የውሃ ሀብቶችን በዘላቂነት ጥቅም ላይ ለማዋል እንዲቻል፣

3.4. በብሔራዊ ደረጃ ወጥ የሆነ የደህንነት ሥርዓት በመዘርጋት የአገልግሎት ጥራቱ የተጠበቀና ደህንነቱ አስተማማኝ የሆነ የውሃ ትራንስፖርት የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ፣

3.5. ሐመር በማምረት ስራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች በተቀናጀ ሁኔታ ተግባራቸውን ለማከናወን የሚችሉበትን የብቃት ማረጋገጫ መለኪያ ደረጃ ማስቀመጥ፣ እንዲሁም ሐመሮች ብቁ የሆኑ እና ደህንነታቸው የተጠበቀ በሆነ ሁኔታ እንዲጠገኑም ሆነ እንዲታደሱ ማስቻል ነው፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የሀገር ውስጥ እና ድንበር ተሻጋሪ ውሃ ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ ለተሰማሩ ባለሞተር ሐመር፣ ሞተር አልባ ሐመር፣ ሐመር አንቀሳቃሾች፣አምራቾች፣ ጠጋኞች እና በማስመጣት ሥራ የተሰማሩ አስመጪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 5. የሀገር ውስጥ ውሃ መንገዶች ምደባ

ለዚህ መመሪያ አላማ ተፈጻሚነት የሀገር ውስጥ የውሃ ላይ መንገድ እንደሚከተለው ይመደባል፡-

5.1.የሀገር ውስጥ የውሃ ወይም የውሃ አካልን የሚያካትት ሲሆን ይህም የውሃ ስፋት፣ ለትራንስፖርትና ለመዝናኛ አገልግሎት መዋልን እንዲሁም ጉዞ የሚያደርግ ሐመር መውሰድ ያለባቸው መሠረታዊ የደህንነት ጥንቃቄን ያጠቃልላል፣

5.2.የተጠቃለለ ውሃ፣ ሌሎች የሀገር ውስጥ የውሃ መንገዶች ወይም አካባቢዎች በእነዚህ ውስጥ በሚንቀሳቀስ ሐመር ከፍተኛ የደህንነት ደረጃዎች ተፈጻሚ የሚሆኑባቸውን ያጠቃልላል፡፡

## 6. በኢትዮጵያ የሀገር ውስጥ ውሃ መንገድ ገደብ

6.1.በኢትዮጵያ የውሃ አካል ክልል ላይ ንብረትነቱ የኢትዮጵያ ከሆኑት ውጭ የትኛውም ሐመር ንግድ ማካሄድ አይችልም፡፡

6.2.ከውጭ/ከጎረቤት መንግሥታት ጋር የሚፈጸም ውል ወይም ስምምነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣የኢትዮጵያ ሐመር ብቻ በኢትዮጵያ የውሃ አካል መንገድ ላይ ንግድ ማካሄድ ይችላሉ፡፡

6.3.በልዩ ሁኔታ ሚኒስቴሩ ወይም በባለስልጣን መ/ቤቱ በጽሁፍ በሚሰጣቸው ትእዛዞች ካልሆነ በስተቀር የኢትዮጵያ ሐመር በባለቤትነት ለመያዝ ያልተፈቀደለት ሰው በማንኛውም ሐመር ተከራይቶ ወይም በሌላ ማንኛውም አግባብ በሀገር ውስጥ የውሃ አካላት ንግድ ለመሰማራት አይፈቀድለትም፡፡

## ክፍል ሁለት
## ምዝገባ፣ደህንነት፣ምርመራ እና ፍተሻ

### 7. የሀመር ማስመዝገብ ግዴታ

ማንኛውም የሐመር ባለንብረት ግለሠብ ወይም ድርጅት ለማንኛውም ተግባር የሚጠቀምበትን ሀመር አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት የማስመዝገብ እና ፈቃድ የማግኘት ግዴታ አለበት፡፡

በዚህ መመሪያ መሠረት በድንበር ተሻጋሪ ወንዞች እና ሃይቆች ላይ በድንበር ተሻጋሪ ውሃ ትራንስፖርት ንግድ የተሰማራ ማንኛውም የሐመር ባለንብረት ግለሰብ ወይም ድርጅት ሐመሩን በኢትዮጵያ ማሪታይም ባለስልጣን የማስመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡

### 8. ለምዝገባ የሚቀርብ ማመልከቻ

8.1.የትኛውም ለሐመር ምዝገባ የሚቀርብ ማመልከቻ በግለሠብ ወይም በድርጅት ሲሆን የሐመሩ ባለንብረት ሆኖ ለመመዝገብ በጠየቀው ሰው፣ በተወካዩ ወይም ሕጋዊ ሰውነት ባለው ድርጅት ወይም በተወካዩ ሊቀርብ ይችላል፡፡

8.2.በመጀመሪያው የሐመር ምዝገባ ላይ በዚህ ርዕስ በተቀመጠው የምዝገባ መስፈርት መሠረት የንብረቱ ባለንብረትነት ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

8.3.ማንኛውም የሐመር ባለንብረት ለመሆን የተፈቀደለት ሰው ሐመሩን በዚህ አንቀጽ መሰረት ማስመዝገብ ይኖርበታል፡፡

8.4.በዚህ መመሪያ ስር የሐመር ምዝገባ ማመልከቻ አመልካቹ የሚከተሉትን የሚገልጽ ማረጋገጫ አያይዞ ማቅረብ አለበት፤ እነዚህም፡-

8.4.1. ሐመሩ በኢትዮጵያ ዜግነት ያለው ሰው ንብረት ወይንም በኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ ድርጅት ንብረት መሆኑ፣

8.4.2. ሐመሩ አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል ሁኔታ ላይ

ስለመሆኑ፣

8.4.3. የሐመሩ አዛዥ ወይም ባህረኞች ዝርዝር እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዝርዝር፣

8.5. በዚህ ቁጥር ስር የተጠቀመው የምዝገባ ማመልከቻ ለሐመሩ መዝጋቢ ሬጅስትራር ወይም በሬጅስትራሩ ፈቃድ/ውክልና ለተሰጠው የሐመር መዝጋቢ መኮንን ይቀርባል፡፡

8.6. ከማረጋገጫው ጋር አመልካቹ የሚከተሉትን ማያያዝ አለበት፡-

8.6.1. ሐመሩን በሰራው አካል የተቀመጠ የሐመሩ ትክክለኛ የመጫን አቅም፣

8.6.2. ሐመሩ የተሰራበት ጊዜ እና ቦታ፣

## 9. በሐመሩ ላይ ምልክት ስለማድረግ

9.1. የሐመሩ ባለንብረት በምዝገባ ወቅት ሐመሩ ለመርማሪው አመቺ ሆኖ በቋሚነት እና በቀላሉ በግልጽ በሚታይ በሚከተለው ሁኔታ ምልክት የተደረገበት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

9.1.1. የሐመሩ ሥም በሐመሩ የፊት አካል ሁለቱም አቅጣጫ፣

9.1.2. የሐመሩ ሥም እና የተመዘገበበት ወደብ በሐመሩ የፊት አካል ሁለቱም አቅጣጫ ጥቁር መደብ በነጭ ወይም በቢጫ ፊደሎች ይፃፋሉ፡፡

9.2. መደበኛ ቁጥሩ እና የሐመሩ የተጣራ ክብደት የሚያመለክተው በሐመሩ ዋና ቋሚ ላይ መመዝገብ አለበት፡፡

9.3. በሐመሩ መዝጋቢ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር የሐመሩ ስም መቀየር የለበትም፡፡

9.4. በኢትዮጵያ የተመዘገቡ ሀመሮች የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ ከሌሎች ባንዲራዎች በስተግራ በኩል፣ የውጭ ሀገር ሀመር ደግሞ የኢትዮጵያን ሰንደቅ አለማን በቀኝ በኩል ማውለብለብ ይኖርበታል፡፡

## 10. የጉዞ ብቁነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

10.1. በሀገር ውስጥ ውሃ የሚንቀሳቀስ ሐመር በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን የሚያረጋግጥ የጉዞ ብቁነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መያዝ ይኖርበታል፡፡

10.2. የጉዞ ብቁነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመገልገያዎችን ዝርዝር እና

ሌሎች ተያያዥ መረጃዎችን የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡

10.3. ሐመሩ በዚህ መመሪያ ቁጥር 10(1) ላይ የተገለጸውን የብቁነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚያገኘው በዚህ መመሪያ ቁጥር 11 መሠረት የፍተሻና ምርመራ ሥርዓት ውስጥ አልፎ ብቁነቱ ሲረጋገጥ ነው፤

10.4. የባሕር ጉዞ ብቁነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት የሚያገለግል ሲሆን ጊዜው ሲያበቃ ለአሰጣጡ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት በሚደረግ ምርመራና ፍተሻ ሊታደስ ይችላል፡፡

10.5. በዚህ መመሪያ ቁጥር 10(4) የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ የምስክር ወረቀቱ በልዩ ሁኔታ ከሶስት ወር ለማይበልጥ ጊዜ ሊራዝም ይችላል ሆኖም ግን የተራዘመበት ምክንያት በምስክር ወረቀቱ ላይ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

## 11. ምርመራና ፍተሻ

በሀገር ውስጥ ውሃ ትራንስፖርት ላይ የሚሰማራ ሐመር ተመዝግቦ ወደ ስራ ከመግባቱ በፊትም ሆነ በዚህ መመሪያ ቁጥር 10(3) መሠረት ወደ ሥራ ከገባ በኋላ በሚከተለው ሁኔታ በምርመራና ፍተሻ ሥርዓት ውስጥ ማለፍ አለበት፡-

11.1. አጠቃላይ ክብደቱ አንድ ቶን ወይም በላይ ወይም ርዝመቱ 3 ሜትር የሆነ የሐመር ባለንብረት በዚህ አንቀጽ መሰረት ሐመሩን ማስመርመር አለበት፡፡

11.2. የሐመሩ ባለንብረቶች ወይም ተወካዩ ሐመሩ ከጭነት ነጻ፣ ጽዱ በሆነ እና በተሟላ ሁኔታ ለምርመራ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

11.3. ለምርመራ አስፈላጊ የሆነውን እገዛ ሁሉ ማድረግ አለበት፡፡ ይህም የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፣

11.3.1. መርማሪ የሚጠቀምበትን ተገቢ ሐመር ማቅረብ፣

11.3.2. ሰራተኞች በምርመራ ጊዜ እንዲገኙ ማድረግ፣

11.3.3. የሐመሩን ዋነኛ አካል ወይም በቀጥታ የማይገኙ ወይም የማይታዩ ክፍሎችን ለምርመራ ማመቻቸት አለበት፡፡

11.4. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ ምርመራውን እና ፍተሻውን በሚከተለው አግባብ ማከናወን ይችላል፡-

11.4.1. ሐመሩን ከውኃ አካል ውጪ በማድረግ መመርመር

11.4.2. የእንቅስቃሴ ላይ ፍተሻ፣

11.4.3. የሐመሩን ዋነኛ አካል ጥንካሬ በሒሳብ ስሌት ማረጋገጥ፣

11.4.4. እንዳስፈላጊነቱ የሐመሩን ያለመናጋት በሒሳብ ስሌት ማረጋገጥ

11.5. በዚህ መመሪያ ቁጥር 11(2) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዴክ አልባ (Open deck) ወይም ለባለ ዴክ ሐመሮዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው ቴክኒካል ፍተሻዎች የሚከተሉትን ያካትታል፡-

11.5.1. ዴክ አልባ (Open deck) ሀመሮች የሚከተሉት መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፤

11.5.1.1. በአደጋ ጊዜ የሕይወት ማዳኛ ላይፍ ጃኬት (ቢያንስ በሚይዙት የሰው ልክ) ፣

11.5.1.2. የህይወት ማዳኛ (በጫፉ ላይ የብረት መንጠቆ ያለው ረዥም ዘንግ)፣

11.5.1.3. የፍሳሽ ማስወገጃ /መዛቂያ (bailer/bucket)፣

11.5.1.4. የመገናኛ መሳሪያዎች (ሬዲዮ፣መስመር አልባ ስልክ፣ሞባይል...ወዘተ)፣

11.5.1.5. የእሳት አደጋ መከላከያና ማጥፊያ መሳሪያ፣

11.5.1.6. የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ መስጫ (First Aid Kit)፣

11.5.1.7. የሐመር መቅዘፊያ

11.5.2. ባለ ዴክ (vessel with separate deck) ሀመሮች የሚከተሉት መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፤

11.5.2.1. የህይወት ማዳኛ (Life Jacket) በሰው ልክ፣

11.5.2.2. የህይወት አድን ቀለበት (Life ring) ፣

11.5.2.3. ከሐመርዋ ላይ ሰው እንዳይወድቅ መከላከያ (Guard rail)፣

11.5.2.4. ከዴክ ወደ ውስጥ የመግቢያ በሮች ውሃ የማያስገቡ (Water tight) መሆናቸውን፣

11.5.2.5. በሞተር ክፍል ተገቢ የእሳት አደጋ መከላከያና ማጥፊያ መኖሩን፣

11.5.2.6. ባትሪዎች በሚገባ መታሰራቸውን፣የሞተር ክፍል ከዘይትና ከናፍጣ ፈሳሽ የጸዳ መሆኑን፣አስተማማኝ የፍሳሽ ማስወገጃ (Bilge pump) በሞተር ክፍል መኖሩን፣

11.5.2.7. የመገናኛ መሳሪያዎች (ሬዲዮ፣መስመር አልባ ስልክ፣ሞባይል)፣

11.5.2.8. በግልጽ በሚታይበት ቦታ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ መቀመጡን፣ መጸዳጃ መኖሩን፣

11.5.2.9. ወደ ሐመር መውጫና መግቢያ ተስማሚና መከላከያ ያለው መሰላል (Gangway) መኖሩን፣

11.5.2.10. የአቅጣጫ መጠቆሚያ ኮምፓስ ወይም GPS መኖሩን፣

11.5.2.11. የተሟላ የመጀመሪያ የህክምና እርዳታ መስጫ (First Aid Kit) መኖሩን፣

11.5.2.12. የተሳፋሪዎች ደህንነት ምቾት በተቻለ መጠን የተሟላ መሆኑን ማረጋገጥ፣

11.6. ምርመራው በባለሥልጣኑ፣ ባለሥልጣኑ ፈቃድ በሰጣቸው ድርጅቶች ወይም በባለሞያዎች ይከናወናል፡፡ ሆኖም በድንበር ተሻጋሪ ውሃ ትራንስፖርት ላይ የተሰማራ ማንኛውም የሐመር ባለንብረት ሐመሩን በኢትዮጵያ ማሪታይም ባለስልጣን የማስመርመር ግዴታ ያለበት ሲሆን ይህም ለክልሎች በውክልና የማይሰጥ ኃላፊነት ነው፡፡ በመመሪያው የተቀመጠውን ቴክኒካዊ መስፈርት ሐመሩ በሙሉ ወይም በከፊል ማሟላቱን የሚያረጋግጥ በማሪታይም አማካሪ ባለሙያዎች የተዘጋጀ የሚጸና ማረጋገጫ የቀረበ ከሆነ መርማሪው ሐመሩን በሙሉ ወይም በከፊል እንዳይመረመር ሊያደርገው ይችላል፡፡

11.7. የሐመሩ መዋቅራዊ ጥንካሬ ወይም የአገልግሎት ሁኔታ በጉልህ የሚቀይር ለውጥ ወይም ጥገና ሲከናወን ሐመሩ ከማናቸውም ተጨማሪ ጉዞ አስቀድሞ በድጋሚ ተገቢውን የምርመራ ሂደት ማለፍ አለበት፡፡ ይህ ምርመራ ከተደረገ በኋላ ከተሻሻለው የሐመሩ ቴክኒካዊ የአገልግሎት ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ለውሃ ላይ ጉዞ ብቁ መሆኑን የሚያመላክት ማረጋገጫ ይሰጠዋል፡፡

## 12. የሕይወት አድን ጥንቃቄዎች እና መሣሪያዎች

12.1. በሌላ ሁኔታ ካልተገለፀ በቀር፣ በነባር ሐመሮች ላይ አዳዲስ የሕይወት አድን መሳሪያዎች ሲተከሉ ተቀባይነት ባላቸው ደረጃ ልክ መሆን አለበት፡፡

12.2. አዳዲስ እና ነባር ሐመሮች የደህንነት እና እርዳታ ለመስጠት የሚያስችል መመሪያዎችን በሚታይ ቦታ መለጠፍ አለባቸው፡፡

12.3. ነባር ሐመሮች ከሚከተሉት የሕይወት አድን መሳሪያዎች ጋር በተገናኘ ያሉ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው፣

12.3.1. የአደጋ ጊዜ ነፍስ አድን ጃኬቶች (LifeJacket)፣

12.3.2. ቀለበታማ መንሳፈፊያ (Life ring/ B u o y )፣

12.3.3. ነፍስ አድን ታንኳ ወይም ሌሎች ለመንሳፈፍ የሚረዱ ቁሳቁሶችን እና የፈሳሽ ማመጣጠኛ መሳሪያዎች፣

12.4. ባለስልጣኑ ነባር ሐመሮች የሚያስፈልጋቸውን ቁሳቁሶች በዚህ መመሪያ መስፈርት መሠረት ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፡፡

12.5. በባለሥልጣኑ በልዩ ካልተፈቀደ በስተቀር ከ70 ሜትር እና በላይ ርዝመት ያላችው ሐመሮች የህይወት አድን ጀልባዎችን(life boat) ወይም ሕይወት አድን መንሳፈፊያዎች (Life raft) መያዝ፣ እንዲሁም ከ 50 ሜትር 69 ሜትር ርዝመት በታች የሆኑ ሐመሮች ደግሞ መንሳፈፊያዎች ሊኖራቸው ይገባል፡፡

## 13. ከሐመር ስለሚወጣ ቆሻሻ

13.1. የነዳጅ ዘይት ቅልቅል፣ ፕላስቲክ፣ ኬሚካል፣ ፈሳሽ ወይም ደረቅ ቆሻሻ ከሐመር ወደ ሀገር ውስጥ የውሃ አካል መልቀቅ ወይም መጣል የተከለከለ ነው፣

13.2. ማንኛውም ከሀመር የሚወጣ ፍሳሽም ሆነ ቆሻሻ በማጠራቀሚያ ተሰብስቦ ወደብ ላይ በተዘጋጀ ማስወገጃ ቦታ ሊሰጥ ይገባል፡፡

# ክፍል ሦሥት
# ሥልጠና እና የሐመር ሰራተኞች ብቃት

## 14. የሐመር ላይ ሰራተኞች ብቃት

14.1. አንድ ግለሰብ የዴክ አልባ ሐመር አዛዥ (Skipper) ለመሆን የሚከተሉት የሥራ ልምዶች ሊኖሩት ይገባል፡-

14.1.1. ሐመር ለማሽከርከር በባለስልጣኑ የተረጋገጠ የብቃት ማረጋገጫ ሊኖረው ይገባል፣

14.1.2. ቢያንስ በቴክኒክ እና ሙያ ወይም አውቶ ሚካኒክ ትምህርት የሠለጠነ ወይም በቂ የሥራ ልምድ ያለው፣

14.1.3. ስለሚሰራበት የውሀ አካል የአየር ሁኔታ ማለትም ነፋስ አቅጣጫ፣

ነፋስና ሞገድ በሐመር እንቅስቃሴ ላይ ስለሚያስከትለው ተፅዕኖ እውቀት ያለው፣

14.1.4. መሠረታዊ የባህር ላይ የሥራ አካባቢ ደህንነት ሥልጠና የወሰደ፣

14.1.5. መንገደኞችን ከመደራረብ አደጋ የመከላከል ግንዛቤ ያለው፣

14.1.6. ስለመንገደኞችና እቃ አጫጫን ግንዛቤ ያለው (Basic stability knowledge)

14.1.7. ስለአካባቢ ብክለት ግንዛቤ ያለው፣

14.1.8. የዳበረ የውሃ ዋና ችሎታ ያለው፣

14.1.9. በሐመር ላይ ለመሥራት የሚያስችል የተሟላ የጤንነት ማስረጃ የሚያቀርብ፣

14.2. የዴክ አልባ ሐመር ሰራተኛ የሚከተሉት የሥራ ልምዶች ሊኖሩት ይገባል፡-

14.2.1. መሠረታዊ የባህረኝነት ሥልጠና የወሰደ፣

14.2.2. የዳበረ የውሃ ዋና ችሎታ ያለው፣

14.2.3. መንገደኞችን ከአደጋ የመከላከል መሰረታዊ ግንዛቤ ያለው፣

14.2.4. ስለአካባቢ ብክለት መሰረታዊ እውቀት ያለው፣

14.2.5. በሐመር ላይ ለመሥራት የሚያስችል የተሟላ የጤንነት ማስረጃ የሚያቀርብ፣

14.3. የባለ ዴክ ሐመር አዛዥ

14.3.1. የባለዴክ ሐመር አዛዥ የሚከተሉትን መስፈርቶች ሊያሟላ ይገባል፡-

14.3.1.1. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ኖሮት በናቪጌሽን የሰለጠነ ወይም በቂ የሥራ ልምድ ያለው፣

14.3.1.2. ስለአጠቃላይ ደህንነት (የእሳት አደጋ መከላከልና ማጥፋት፣ ስለመጀመሪያ ህክምና እርዳታ አሰጣጥ፣ በአደጋ ጊዜ ስለሚወሰዱ የህይወት ማዳኛ ዘዴዎች…ወዘተ) ልምድ ያለው

14.3.1.3. ስለሐመር አያያዝ (seaman ship) በቂ እውቀት ያለው

14.3.1.4. የሀገር ውስጥ ውሃ ትራንስፖርት ናቪጌሽን (ቻርት፣ስለውሃ ሞገድ/ከረንት፣ ማእበል፣ ኮምፓስ፣ ስለ አየር ጠባይ …ወዘተ እውቀት እና ልምድ ያለው፣

14.3.1.5. ስለመገናኛ መሳሪያዎች አጠቃቀም እውቀት ያለው፣

14.3.1.6. መንገደኞችን ከመደራረብ አደጋ የመከላከል ግንዛቤ ያለው፣

14.3.1.7. የመንገደኛ፣እቃ አጫጫን እና ደህንነት(Boat safety and stability) እውቀት ያለው፣

14.3.1.8. ስለመልህቅ (anchor) አጣጣልና አነሳስ እውቀት /ልምድ ያለው፣

14.3.1.9. ስለአካባቢ ብክለት በቂ እውቀት ያለው፣

14.3.1.10. በሐመር ላይ ለመሥራት የሚያስችል የተሟላ የጤንነት ማስረጃ የሚያቅርብ፣

14.4. የባለዴክ ሐመር ሰራተኛ ቢያንስ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

14.4.1. መሰረታዊ የባህረኝነት ሥልጠና የወሰደ፣

14.4.2. የሐመር ጠቅላላ እውቀት (ስለገመድ አስተሳሰር፣ መሪ መያዝ፣ ስለቻርት፣ ስለኮምፓስ፣ ስለደህንነት ስለቀለም አቀባብ….ወዘተ)

14.4.3. ስለሐመር አመራር (navigation) መጠነኛ እውቀት ሊኖረው ይገባል፡፡

14.4.4. ስለመንገደኞች እና ስለእቃ አጫጫን መሰረታዊ ግንዛቤ ያለው፣

14.4.5. ስለአካባቢ ብክለት በቂ እውቀት ያለው፣፣

14.4.6. በሐመር ላይ ለመሥራት የሚያስችል የተሟላ የጤንነት ማስረጃ የሚያቀርብ፣

14.5. የውስጥ ሞተር(inbuilt motor) የተገጠመላቸው ሐመሮች ላይ በምህንድስና /በቴክኒሻን/ በመካኒክነት የሚመደበው ሰው የሚከተሉት ሥልጠና እና የሥራ ልምድ ሊኖረው ይገባል፡፡

14.5.1. መሠረታዊ የባህረኛኝነት ሥልጠና (መሠረታዊ የእሳት መካላከልና ማጥፋት ሥልጠና፣የመጀመሪያ የህክምና እርዳታ አሰጣጥ ሥልጠና ያለው)፣

14.5.2. በምህንድስና፣ በደረጃ 3 ቴክኒክ እና ሙያ ወይም በጠቅላላ ሜካኒክነት የሠለጠነ ወይም በቂ የሥራ ልምድ ያለው፣

14.5.3. ስለባህር አካባቢ ብክለት በቂ ግንዛቤ ያለው፣

14.5.4. በሐመር ላይ ለመሥራት የሚየስችል የተሟላ የጤንነት ማስረጃ የሚያቀርብ፣

## 15. ስልጠና እና ልምድ

15.1. የብቃት ደረጃን ለማሟላት የሚያስፈልግ ንድፈ ሃሳባዊ እውቀት፣ አረዳድ እና ብቃትን የሚያረጋግጥ ሥልጠና እና የሥራ ልምድን በተመለከተ

በሚመለከተው በባለሥልጣን መ/ቤት የሚዘጋጅ እና በማሠልጠኛ ተቋማት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

15.2. እያንደንዱ እጩ የሀገር ውስጥ ትራንስፖርት ባለሙያ በባለሥልጣኑ የተረጋገጡትን የሥልጠና ፕሮግራሞች በሐመር ላይ ያለ ሥልጠናን ጨምሮ መከታተል ይኖርበታል፣ ይህም

15.2.1. በሀገር ውስጥ ውሃ አገልግሎት እያንዳንዱ እጩ ባለሙያ የስራ ሀላፊነቱን እና ተግባሩን በተግባር ሥልጠና እና ልምድ መቅሰሙን ማረግገጥ፣

15.2.2. በሐመር ላይ የጸደቀው የሀመር ላይ የተግባር ስልጠና ብቃታቸው በተረጋገጡ ባለሙያዎች የቅርብ ክትትል እና ቁጥጥር መደረጉ፣

15.2.3. በሥልጠና መመዝገቢያ ወይንም በተመሳሳይ ሰነዶች ላይ መመዝገቡን፣ የሚያረጋግጥ መሆን አለበት፡፡

15.3. ሥልጠናው እና ልምዱ ተገቢነት ያላቸው የብቃት ማረጋገጫ ደረጃዎች መሟላታቸውን ያረጋገጠ ይሆናል፡፡

## 16. የደህንነት ሥልጠና

እያንዳንዱ በሐመር ላይ የተለያዩ የስራ ተግባራቶችን የሚያከናውን ሰው ከታች በተገለጸው በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ያለውን የደህንነት ሥልጠና መውሰድ ይኖርበታል፡፡

16.1. እያንዳንዱ የሐመር ሰራተኛ ለስራ ከመመደቡ በፊት ራስን ከአደጋ ለመከላከል የሚያስችል መሰረታዊ የደህንነት ሥልጠና መውሰድ ወይም የሚከተሉትን ለመፈጸም በቂ መረጃ እና ትእዛዝ መቀበል የሚችል መሆኑ መረጋገጥ አለበት፣

16.1.1. ከሌሎች ሐመሮች ላይ ከሚገኙ ሰዎች ጋር መሰረታዊ በሆኑ በደህንነት ጉዳዮች መረጃ መለዋወጥ መቻል እና የደህንነት መረጃ መልእክቶች፣ ምልክቶችን እና የድምጽ ምልክቶችን መረዳት፣

16.1.2. ሰው ዉሃ ላይ በሚወድቅ ጊዜ፣ እሳት ወይም ጭስ ሲታይ ወይም የእሳት ወይም ሐመር ጥሎ የመውጣት አደጋ ደወል ሲሰማ መደረግ ያለበትን ማወቅ፣

16.1.3. የአደጋ ወይም አጣዳፊ ጊዜ መሰባሰቢያ እና በአደጋ ጊዜ መውጫ በሮችን መለየት ጠንቅቆ ማወቅ፣

16.1.4. የነፍስ አድን ጃኬት የሚቀመጥበትን ቦታ እንዲለይ እና እንዲለብሱ ማድረግ፣

16.1.5. በአደጋ ጊዜ ደወል መጠቀም እና መሰረታዊ ተንቀሳቃሽ የእሳት መከላከያ መሳሪያ አጠቃቀም እውቀት እንዲኖር ማድረግ፣

16.1.6. አደጋ ወይም ድንገተኛ የጤና እርዳታ የሚያስፈልግ ሁኔታ ሲከሰት ተጨማሪ የህክምና ድጋፍ ከመጠየቁ በፊት ወዲያውኑ የመጀመሪያ እርዳታ መስጠት እንዲችል ማስቻል፣

16.1.7. ሐመሩ ላይ ከውሃ አካል በላይ የተገጠሙ የእሳት አደጋ በሮችን እና የውሃ ስርገት መከላከያ በሮችን መክፈት እና መዝጋት መቻል አለበት፡፡

15.2. በየትኛውም ደረጃ በእንቅስቃሴ ላይ ባለ ሐመር በደህንነት እና ብክለት መከላከል ሥራ ላይ የሐመር ሰራተኛ ቡድን አባል ሆነው ተመድበው የሚሰሩ በሐመሩ የትኛወም ሥራ ላይ ከመመደባቸው በፊት ራስን ከአደጋ የማዳን ቴክኒክ፣ የእሳት አደጋ መከላከል እና መቆጣጠር፣ መሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ፣ የግል ደህንነት እና ማህበራዊ ኃላፊነት ተገቢነት ያለው መሰረታዊ ሥልጠና መውሰዳቸውን የሚረጋግጥ የምስክር ወረቀት ሊይዙ ይገባል፡፡

## ክፍል አራት

## 17. ተሳፋሪዎች እና ጭነትን ስለማጓጓዝ

በባለሥልጣኑ ወይም ውክልና በተሰጠው የክልል ቢሮ በግልፅ ፍቃድ ካልተሰጣቸው በስተቀር በሞተር ሀይል የማይንቀሳቀሱ ሐመሮች ከ 6 ተሳፋሪ ወይም 500 ኪሎ የጭነት በላይ መጫን አገልግሎት ስራ ላይ መሰማራት አይችሉም፡፡

17.1. በመንገደኞች ሐመር ወይም የጭነትና መንገደኞች የሚሳፈር ከፍተኛው የመንገደኛ ቁጥር ሐመሩ ለውሃ ላይ ጉዞ ብቁ መሆኑን የሚያረጋግጥ ምስክር ወረቀት ላይ ከተገለፀው መጠን በላይ መሆን የለበትም፡፡

17.2. በተለዩ የመጫኛ ስፍራዎች እንዲጫን የተፈቀደውን ከፍተኛ የተሳፋሪዎች ብዛት እና ጭነት ልክ የሚያሳይ ማስታወቂያ በእያንዳንዱ የሐመር ወለል እና የመጫኛ ስፍራ ላይ በግልፅ

መለጠፍ አለበት፡፡

## 18. ከፍተኛ የተሳፋሪዎች ቁጥር

18.1. በመንገደኞች ሐመር ወይም የጭነት እና መንገደኞች ሐመር እንዲጫን የተፈቀደ ከፍተኛ የተሳፋሪ ቁጥር እንደተገቢነቱ በሂሳብ ስሌት ወይም በሐመሩ ያለመናጋት ማረጋገጫ ምዘና (stability proof test) ይለያል፡፡ ይህም በባለሥልጣኑ መስፈርት መሠረት የተፈቀደ ዝቅተኛ የጭነት ስፍራን (Freeboard) ያመላክታል፡፡ በሐመሩ ማሳፈሪያ ወለሎች (Deck) እና በሌሎች የተለዩ ስፍራዎች እንዲጫን የተፈቀደ ከፍተኛ የተሳፋሪዎች ቁጥር በመገልገያዎች ዝርዝር እና ሐመሩ መረጃ ላይ መስፈር ይኖርበታል፡፡

18.2. ሐመር በባለሥልጣኑ የተቀመጠለትን የተሳፋሪ እና ጭነት ጥምርታ አክብሮ መንቀሳቀስ በመገልገያዎች ዝርዝር እና በሐመሩ መረጃ ላይ መስፈር ይኖርበታል፡፡

## 19. እቃዎችን በብትን እና አደገኛ እቃዎችን ስለማጓጓዝ

19.1. እቃን በብትን መጫን በመንሸራተት ምክንያት ከፍተኛ አደጋ ሊያመጣ ስለሚችል ከዚህ በታች የተገለፁትን ብትን እቃዎች የሚጭኑ ሐመሮች በባለሰልጣን መ/ቤቱ በሚወጡ መስፈርቶች የሚያሟሉ እና ባለሥልጣኑ የሚጠይቃቸውን ተፈጻሚነት ያላቸው ቅድመ ሁኔታዎች የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡

19.1.1. ብትን የእህል ጭነት፣ብትን ጭነት እና በእሽግ መልኩ
19.1.2. የቁም እንስሳት
19.1.3. በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማጓጓዝ አደገኛ ተብለው የተለዩ እቃዎች

19.2. በዚህ መመሪያ ቁጥር 19.1 ላይ የተገለጸው ቅድመ ሁኔታ በባለስልጣኑ የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡

## 20. በአደጋ ጊዜ ግዴታዎች እና ሪፖርት ማድረግ

20.1. የሐመር አዛዥ በሀገር ውስጥ ውሃ ላይ አጣዳፊ ሁኔታ የገጠመውን ወይም ጉዳት የደረሰበትን ሌላ ሐመር ወይም ሰው የመርዳት/የማገዝ ግዴታ አለበት፣

20.2. በሐመር ላይ የሰው ሕይወት መጥፋት ወይም በሐመሩ ላይ አካላዊ ጉዳት፣ ሐመሩ መንቀሳቀስ በማይችልበት ሁኔታ መሆን፣ ሀመሩን ትቶ መሸሽ ወይም መጥፋትን ያስከተለ አደጋ ወይም ጉዳት በተከሰተ ጊዜ

የሐመሩ ባለንብረት ወይም አዛዥ ለባለሥልጣኑ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

20.3. ለባለሥልጣኑ በቀጥታ ማሳወቅ የማይቻል ከሆነ በቅርብ ላለ መርማሪ፣ የሐመር መዝጋቢ፣ የፖሊስ አባል ወይም የወደብ ኃላፊ መረጃውን መስጠት አለበት፡፡ እነዚህም ስለሁኔታው ወዲያውኑ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

20.4. ከሐመሩ ላይ ሰው ከሞተ ወይም ከሀመሩ መጥፋት በሚከሰትበት ጊዜ ለባለሥልጣኑ የሚሰጠው መረጃ ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡፡

20.4.1. የአደጋው ወይም ክስተቱ አይነት፣ቀን፣ሰዓት እና ቦታ፣

20.4.2. የእያንዳንዱ የሞተ ወይም የጠፋው ሰው ሥም፣

20.4.3. የሐመሩ መለያ ቁጥር ሥም እና የተመዘገበበት ወደብ እና

20.4.4. የሐመሩ ባለንብረት ሥም እና አድራሻ

20.5. በባለሥልጣኑ የሚፈለገው መረጃ በሚከተለው ሁኔታ መሰጠት አለበት፣

20.5.1. አደጋው ወይም ጉዳቱ በተከሰተ በ48 ሰዓት ውስጥ፣ ሰው ከሞተ ሁኔታው በተከሰተ በ24 ሰዓት ውስጥ፣ ከመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ ያለፈ የህክምና እርዳታ የሚያስፈልግበት ሁኔታ ከተከሰተ ወይም ሰው የጠፋ እንደሆነ፣ ወይም

20.5.2. ቅድሚያ የማሳወቅ ግዴት የሌለ እንደሆነ ክስተቱ ባጋጠመ በ10 ቀናት ውስጥ

20.6. ለባለሥልኑ የሚሰጠው መረጃ በፅሁፍ የተደረገ፣ ቀን የተፃፈበት እና ባዘጋጀው ወይም ባዘጋጁት ሰዎች የተፈረመ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ማረጋገጫ መሆን አለበት፡፡

## 21. የአደጋ ምርመራ ማድረግ

20.1. በሐመሩ ወይም በሐመር አካላት ላይ አደጋ ወይም ጉዳት ሲደርስ እና በውጤቱም ከዚህ በታች የተጠቀሱት ከተከሰቱ ህጋዊ ምረመራ በባለሰልጣን መ/ቤቱ ይደረጋል፡፡

21.1.1. የሰው ሕይወት ሲያልፍ፣

21.1.2. በሰው ላይ የአካል ጉዳት ሲደርስ እና ጉዳቱም ከመጀመሪያው ደረጃ የህክምና እርዳታ ያለፈ ሲሆን፣

21.1.3. ሰው ከሐመሩ ላይ ሲጠፋ እና የመሞት ወይም የአካል ጉዳት የማጋጠም እድል የሰፋ ከሆነ ወይም

21.1.4. ሐመሩ ላይ ወይም ሌላ ንብረት ላይ ጉዳት ሲደርስ፡፡

## ክፍል አምስት

## ሐመር በማምረት፣ በመጠገን እና በማስመጣት ሥራ ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

### 22. ችሎታ የማረጋገጫ መመዘኛ መስፈርቶች

ማንኛውም ሐመር በማምረት፣በመጠገን፣በማስመጣት የንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት የፈለገ ድርጅት/ሰው የብቃት ማረጋገጫ ከባለሥልጣኑ ማግኘት አለበት፤ ብቃቱን ለማረጋገጥ ሚከተሉትን ሂደቶች መከተል አለበት፡-

22.1. በሐመር ማምረት ወይም ጥገና ላይ ወይም በሁለቱም የሚሰማራ ድርጅት የድርጅቱ ባለቤት (አመልካች) ወይም የሚቀጥረው አሰሪ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተገቢው ክህሎት እና የሥራ ልምድ እንዲሁም ዘርፉ የሚጠይቀውን የትምህርት ዝግጅት ማሟላት ይጠበቅበታል፡-

22.1.1. ከታወቀ ዩኒቨርስቲ ወይም ኮሌጅ )፣ናቫል አርክቴክት (Naval Architect)፣ በስትራክቸራል መኀንዲስነት (Structural manager) በናቪጌሽን (nautical science)፣ በመርከብ ዲዛይን፣ በማሪን ኢንጂኔር (Marine Engineer)፣ በኤሌትሪክ መኀንዲስነት (Electrical engineer)፣ መኀንዲስ ማናጀርነት (Engineering manager)፣ ጀነራል መካኒክነት (General mechanics) ወይም ተዛማጅ በሆኑ የትምህርት መስኮች ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው እና የብቃት ማረጋገጫ በጠየቀበት ዘርፍ አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ያለው/ያላት በሀላፊነት፤

22.2. በዚህ መመሪያ ቁጥር 22.1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሐመር በማምረት እና ጥገና ስራ የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጠው የሚያመለክት ድርጅት/ሰው በስሩ ስራውን የሚያከናውኑለት የሚከተሉት ሰራተኞች ይኖሩታል፡-

22.2.1. የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጠው ያመለከተው ሰው ድርጅቱን በበላይነት ለመምራት የሚችል ከላይ የተዘረዘሩትን ለዘርፉ አግባብነት ያለውን የትምህርት ዝግጅት፣ ክህሎት እና የስራ ልምድ ያለው የበላይ ኃላፊ ሊኖረው ይገባል ሆኖም ግን አመልካቹ ካላይ የተዘረዘሩትን ክህሎት፣ የትምህርት ዝግጅት እና የሰራ ልምድ የሚያሟላ ሆኖ ከተገኘ ደርጅቱን በበላይ ሀላፊነት ሊመራ ይችላል፡፡

22.2.2. በበላይ ኃላፊው ስር ስራውን የሚያከናውኑ የሚከተሉት ሰራተኞች ይኖሩታል፡-

22.2.2.1. ማናጀር

22.2.2.2. ናቫል አርክቴክት ወይም ስትራክቸራል መሃንዲስ ሺፕ ማስተርነት ወይም ኔውቲካል ባለሙያ

22.3. የቢሮ አደረጃጀት በቴሌፎን፣ ፋክስ፣ የሂሣብ መመዝገቢያ ማሽን፣ የጽህፈት መሳሪያዎች እንደ ኮምፒውተር፣ ፎቶ ኮፒ፣ ፕሪንተር ወ.ዘ.ተ. ያሟሉ በአግባቡ የተደራጀ ቢሮ መሆን አለበት፣

22.4. ድርጅቱ ስራውን ለማከናወን ደረጃውን የጠበቀ ሐመሮችን ለመጠገን እና ለማደስ የሚያስችል በቂ ቦታ ሊኖረው ይገባል፣

22.5. ድርጅቱ ስራውን ለማከናወን ቢያንስ የሚከተለው የማምረቻ ማሽኖች (Deck Machineries) ሊኖረው ይገባል፡-

22.5.1. ጠፍጣፋ ብረቶችን ለመቁረጥ የሚረዳ ማሽን(Automatic flame cutter for steel plate)፣

22.5.2. ጠፍጣፋ ብረቶችን ለማጠፍ እና ቅርፅ ለማስያዝ የሚረዳ ማሽን (Electrical arc welding machine for bending and welding steel sheet)፣

22.5.3. የዝገት ማስወገጃ ማሽን (Blasting machine)፣

22.6 ድርጅቱ ስራውን ለማከናወን የሚከተለው ገንዘብ ካፒታል ሊኖረው ይገባል፡-

22.6.1 በሥራ መስኩ ላይ ለመሰማራት 1 ሚሊየን ብር ካፒታል ያስፈልጋል፡፡

22.6.2 አመልካች በተጠቀሰው የሥራ ዘርፍ የሚያስፈልገው የገንዘብ ካፒታል ግማሹን የሚያሳይ የባንክ ደብዳቤ እና የ3 ወር የባንክ ስቴተመንት (statement) ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

22.6.3 በሥራ መስኩ ላይ የተሰማራ ድርጅት 500 ሺ ብር በቢሮ እና ለቢሮ አደረጃጀት በአይነት ማሰየት አለበት፡፡

22.7 ድርጅቱ የንግድ ማህበር ከሆነ በተገቢው የፍትህ አካል የፀደቀ የማህበሩን መመስረቻ ፅሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

22.8 የባለሞተር ሐመሮችን ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባት ስራ ላይ ለመሰማራት የሚጠይቅ አመልካች የሚያስገባው የሐመር አይነት የሀገር ውስጥ ውሃን ለብክለት የማይዳርግ የሠራተኞችንና የተሳፋሪዎችን ደህንነት በተገቢው መልኩ የሚያረጋግጥ መሆን ይኖርበታል፡፡

22.9 ለውሃ ላይ ትራንስፖርት አገልግሎት እና ለሌላ የተለያየ አገልግሎት ከውጪ ሀገር ወደ ሀገር የሚገቡ ሐመሮች ከላይ በንኡስ ቁጥር 22.8 እና በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላቱን በማሪታይም ዘርፍ በተሰማሩ አማካሪ ድርጅቶች መረጋገጥ አለበት፡፡

22.9.1 ሐመሩ የት እና ምን በሚባል ድርጅት እንደተሠራ የሚያረጋግጥ የሐመር ግንባታ ሰርተፊኬት፤

22.9.2 ሐመሩ ለማንቀሳቀስ የተገጠሙ ማሽነሪዎች ደህንነት ማረጋገጫ (ሰርተፊኬት)፣

22.9.3 የሐመሩ ጠቅላላ፣ ርዝመት፣ ስፋትና ጥልቀት፣

22.9.4 የሐመሩ ክብደት፣የመጫን አቅም/ተሳፋሪ ወይም እቃ/፣

22.9.5 የህይወት ማዳኛ ጃኬት እና የመገናኛ መሳሪያ ብዛትና ይዘት፣

22.9.6 ሐመሩ የሚያስገባው ባለቤት ስም፣ አድራሻና ሐመሩ አገልግሎት የሚሰጥበት የሥራ ቦታ፣

22.9.7 የሐመሩ የሞተር አይነትና የፈረስ ጉልበት፣

22.9.8 ሐመሩ ለምን አገልግሎት እንደተሰራ፣

22.9.9 ሞተሩን የሰራው ድርጅትና የሞተሩ ሞዴል፣

22.9.10 ሐመሩ ውሃ ላይ ሚዛኑን ጠብቆ የመንሳፈፍ ብቃቱ የተፈተሸበት ሰነድ /stabilitydocuments/

22.9.11 ባለቤትነት ማረጋገጫ ከግዢ ውል /bill of sale/ ጋር በማያያዝ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## 23. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

23.1. ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ተግባር በመዝጋቢው አካል በተዘጋጀ ቅፅ ተሞልቶ ይቀርባል፡፡

23.2. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለእያንዳንዱ አመልካች የሚከተሉትን ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፣

23.2.1. የተመዘገቡ ሙያተኞች እና መሳሪያዎች፣ ቁጥር እና ዓይነት፣

23.2.2. ዓመታዊ የክንውን ሂሳብ፣

23.2.3. አግባብ ባለው አካል የተደረገ የክዋኔ ግምገማ የተሰጠ ውጤት፣

23.2.4. ሌሎች በዚህ መመሪያ መሰረት ሥራውን ለመወጣት የሚያስፈልጉ አግባብነት ያላቸው ሰነዶች፡፡

## 24. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት

24.1. በዚህ መመሪያ መሠረት አመልካቹ የተደነገገውን አሟልቶ ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሲያቀርብ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ይሰጣል፡፡

24.2. ብቃት የምስክር ወረቀቱን መስጠት ያልተቻለ እንደሆነ አመልካቹ ማሟላት ያለበትን እና አግባብነት ያላቸውን እርምጃዎች በፅሁፍ እንዲያውቅ ይደረጋል፡፡

24.3. አመልካቹ የተቀመጡ መስፈርቶችን ሙሉ በሙሉ ማሟላት ካልቻለ ባለሰልጣኑ ጊዜያዊ ምስክር ወረቀት በመስጠት ያልተሟሉት እንዲሟሉ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 25. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዕድሳት

25.1. በዚህ መመሪያ ቁጥር 24 መሰረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለአንድ ዓመት ፀንቶ የሚቆይ ሲሆን የኢትዮጵያ በጀት ዓመት ካለቀ በኋላ በሚቀጥሉት ሁለት ወራት ውስጥ መታደስ አለበት፡፡

25.2. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚታደሰው ድርጅቱ በዚህ መመሪያ መሠረት የሥራ አፈፃፀም መሟላቱ ከተረጋገጠ በኋላ ነው፡፡

25.3. በዚህ እንቀጽ ንዕስ አንቀፅ 25.2 መሰረት የተገለፁ መስፈርቶች ተሟልቶ ካልተገኘ የዕድሳት ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ በአስር ቀናቶች መውሰድ ያለበትን አግባብነት ያላቸውን እርምጃዎች በፅሁፍ ያሳውቀዋል፡፡

## 26. ፍቃድ ስለመሰረዝ

26.1. ባለሥልጣኑ ማንኛውንም በአገር ውስጥ ውሃ ትራንስፖርት የተሰማሩ ሐመሮች የስራ ፈቃዳቸውን በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊሰርዝባቸው ይችላል፡-

26.1.1. ይህ ፈቃድ የተሰጠው ሐመር ወደ ውሃ አካል ገብቶ ለመንቀሳቀስ ብቁ ሳይሆን ሲቀር፣ አገልግሎት መስጠት ሲያቆም፣ በሐይቅ ወይም በወንዝ አካባቢ ለብክለት ምንጭ እንደሆነ ወይም ተጠቃሚዎችን ለአደጋ በሚያጋልጥ መንገድ የሚሰራ ከሆነ፣ ሌሎች ጀልባዎችን ለችግር የሚዳርግ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

26.1.2. ጀልባው ለሌላ ወገን ተላልፎ እንደሆነ፣ ከተሸጠ ወይም ከተወገደ ወይም ባለሥልጣኑ በቁጥጥር ወቅት ፈቃዱ የተጠቀሰው ጀልባ ስራውን ማቆሙን ካረጋገጠ፤

26.1.3. ፈቃድ የተሰጠው ሐመር በህገወጥ ተግባር ተሰማርቶ ከተገኘ እና በሚመለከተው አካል ወንጀል መፈጸሙ የተረጋገጠ እንደሆነ፤ ወይም

26.1.4. በማናቸውም የማመልከቻ ቅጽ የቀረበ ማንኛውም መረጃ የተሳሳተ ነው፡፡

26.2. በዚህ መመሪያ መሠረት ባለሥልጣኑ ማንኛውንም ፈቃድ የሰረዘ እንደ ሆነ፣ ባለስልጣኑ ወይም የወደብ አስተዳደሩ ወዲያውኑ መሰረዙን ለባለፈቃድ ሰጪው በማመልከቻው ቅጽ ላይ በተገለጸው አድራሻ በጽሑፍ ማስታወቅ አለበት፡፡

# ክፍል ስድስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 27. አስተዳደራዊ እርምጃ

27.1. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በማጭበርበር ወይም የተጭበረበሩ ሰነዶችን መሠረት ተደርጎ የተገኘ ከሆነ ወይም የምስክር ወረቀቱን የያዘው ሰው ይህንን መመሪያ የሚፃረር ተግባር በመፈጸሙ ተከሶ ከተፈረደበት ወይም በምርመራና ፍተሻ የተገኘበትን ጉድለት በተሰጠው ጊዜ ሳያርም ቢቀር ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡

27.2. በቁጥር 27(1) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ በክልል የሚገኙ የሀመር አንቀሳቃሾች፣ አምራቾች፣ ጠጋኞች በዚህ መመሪያ የተከለከሉ ድርጊቶችን

ከፈጸሙ ወይም እንዲሟሉ የሚጠበቁ ሁኔታዎችን ሳያሟሉ ቢገኙ የሚመለከተው የክልል ቢሮ በሚያጸድቀው የቅጣት ታሪፍ መሠረት የገንዘብ ቅጣት ሊቀጣ ወይም አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

## 28. የሀገር ውስጥ ውሀ ወደብ ሀላፊነት እና ተግባር

28.1. የሀገር ውስጥ ውሀ ወደብ እንደአስፈላጊነቱ የወደብ አስተዳዳሪ እና ባለሙያዎች/ሰራተኞች፣ የወደብ ፋሲሊቲ ማለትም የወደብ አስተዳደር ቢሮ፣ የሐመር መጠገኛ ቦታ፣ የመንገደኞች ማረፊያ፣ የእቃ መጋዘን፣የሐመር መጠጊያዎች፣ መዝናኛ፣ መጸዳጃ ፣ አረንጓዴ ቦታ እና የመሳሰሉት ሊኖረው ይገባል፣

28.2. ማንኛውም ወደብን የሚያስተዳድር አካል የሀገር ውስጥ ውሃ ወደቡ እና በመዳረሻ ውሃ አካላት ላይ የትራፊክ፣ ደህንነት፣ ጸጥታ እና የአካባቢ ብክለትን ለመከላከል የሚያስችል ህግ የማውጣት እና ክትትል የሚያደርግ አካል መመደብ እና መተግበር እንዲሁም የወጣውን ህግ ባለስልጣን መ/ቤቱ ማሳወቅ አለበት፣

28.3. በወደብ፣ በወደብ መዳረሻ መልህቅ ጥለው እንዲሁም ወደብ አካባቢ ያሉ ሐመሮችን ደህንነት፣ ጸጥታ እና የውሃ አካለቱን አካባቢ ጥበቃ የመቆጣጠር ግዴታ አለበት፣

28.4. ወደብ የሚያስተዳድር አካል ለወደብ ሰራተኞች እና ዋና ዋና ተጠቃሚዎች የወደብ ደህንነት ስልጠና እና ልምምድ መስጠት ይኖርበታል፣

28.5. ወደብ ላይ የእሳት መከላከያ፣ የነብስ አድን ቀለበት፣ መጀመሪያ እርዳታ መስጫ መሳሪያ እና የደህንነት ምልክቶች የሚገባቸው ቦታ ላይ ማስቀመጥ አለበት፣

28.6. ወደብ የሚጠቀሙ ሐመሮች በሚመለከተው አካል የተመዘገቡ እና አመታዊ ፍተሻ የተደረገላቸው መሆኑን የማረጋገጥ እና ያላሟሉ በቅጣት ባሉበት እንዲያሟሉ የማድረግ ግዴታ አለበት፣

28.7. ሐመር ተቀጣጣይ የሆነ እቃ ይዞ የሚመጣ ከሆነ በቅድሚያ እንዲያሳውቅ እና የቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፣ ሐመር ተቀጣጣይ እቃ በሚጭንበት ጊዜ አስፈላጊው ጥንቃቄ መደረጉን ማረጋገጥ አለበት፣ የደህንነት መሳሪያዎች መቅረባቸውን እና ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ሰዎች ብቻ የጥንቃቄ ግንዛቤ ወስደው እንዲሳተፉ ማደረግ አለበት፣

28.8. ከሐመር ለመውረድም ሆነ ወደ ሐመር ለመውጣት በሐመር መጠጊያ

እና በሐመር መካከል ደህንነቱ የተጠበቀ መተላለፊያ መሰላል ወይም ተመሳሳይ ዘዴ መጠቀም አለበት፣ ይህ ባልተሟላበት ሁኔታ ሰው እንዳይጠቀም መከልከል አለበት፣

28.9. ባለወደብ አካል ወደቡ አካባቢ የሚከሰት አደጋን መመዝገብ፣ መመርመር እና የሰው ህይወት ከጠፋ፣ ሰው ወይም ሐመር ከጠፋ፣ በሰው ወይም ሐመር ላይ ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 29. የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለስልጣን ሀላፊነት ተግባር

ይህንን መመሪያ በተመለከተ የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 549/1999 ዘርፉን ለመቆጣጠር በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለው ሀላፊነት ይኖረዋል፡፡

29.1. የብቃት ማረጋገጫ ደረጃ በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይቆጣጣራል እንዲሁም ያሻሽላል፡፡

29.2. የቁጥጥር ስርዓቱ ውጤታማ እንዲሆን በስርዓቱ ሚና ያላቸው አካላትን ያቀናጃል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል፡፡

29.3. የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ማመልከቻ ላቀረበ አመልካች ድርጅት በዚሁ መመሪያ መሠረት መስፈርቶች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ወደ ሥራ ለመሰማራት የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

29.4. ባለሥልጣኑ በውስጥ እቅዱ እና ፕሮግራሙ መሠረት ቀደም ሲል መስፈርቱን አሟልተው የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ የቀላል ሐመር ጠጋኝ እና አዳሽ ድርጅቶችን ድንገተኛ ምልከታ በማድረግ ብቃታቸውን ለማረጋገጥ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፡፡

29.5. ባለሥልጣኑ በሚያደርገው ቁጥጥር፤ እንደየሙያዊ ስነ-ምግባር መጣስ፣ ለስራው ብቁ ያለመሆን በጥንቃቄ መጉደል ምክንያት በደንበኞች ላይ ጉዳቶችን ማድረስ፣ በካፒታልነት ሊኖሩ የሚገቡ ዓይነት እና የጥሬ ገንዘብ መጉደል የሆኑ መሠረታዊ ጉድለቶች ሲያገኝ የሰጠውን ሐመር የመጠገን እና የማደስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰርዛል፡፡

29.6. ባለሥልጣኑ ቀላል ሐመር በመጠገንና እና በማደስ ስራ የተሰማሩ ደርጅቶችን የብቃት ማረጋገጫ የሰረዘ እንደሆነ የተሰረዘበትን ምክንያት በዝርዝር በፅሁፍ ለድርጅቱ ያሳውቃል፡፡

29.7. ባለሥልጣኑ ቀላል ሐመር በመጠገን እና በማደስ ስራ የተሰማሩ

ድርጅቶችን የብቃት ማረጋገጫ የሰረዘ እንደሆነ ውሳኔውን ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፡፡

29.8. ባለሥልጣኑ በአዋጁ የተደነገጉትን ሥራዎች በተለይም ሐመሮችን ምዝገባና፣ የደህንነት ቁጥጥርና መሰል ተግባራትን ለክልሎች ወይም ለሦስተኛ ወገን ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 30. የሚኒስቴሩ ተግባር እና ኃላፊነት

30.1. ሚኒስቴሩ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 29 መሠረት በባለሥልጣኑ ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ ይግባኞችን መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ የሚሰጥ ኮሚቴ በሥሩ ያዋቅራል፡፡

30.2. ይህ የተዋቀረው ኮሚቴ ይግባኞችን ይቀበላል፣ የሚያስቀርቡ እና የማያስቀርቡ ይግባኞችን ይለያል፣ በሚያስቀርቡ ይግባኞች ላይ ተገቢውን ምርምራ ያካሂዳል፣ መቅረብ ያለባቸው ማስረጃዎችን እንዲያቀርቡ ያዛል፣ ውሳኔው ተገቢ ነው ብሎ ካመነ የባለሥልጣኑን ውሳኔ ያጸድቃል፣ የባለሥልጣኑ ውሳኔ ተገቢ አይደለም ብሎ በአመነ ጊዜ በባለሥልጣኑ የተሰጠውን ውሳኔ ይሽራል ይኸም በሚኒስቴሩ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## 31. የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት

31.1. ባለሥልጣኑ ለሥራው ብቁ አይደላችሁም ሲል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከመስጠቱ በፊት የተወሰነባቸው ወይም የብቃት ማረጋገጫ ከተሰጣቸው በኋላ በተደረገ ቁጥጥር የተወሰነባቸው ባለጉዳዮች በተሰጠው ውሳኔ ቅር ከተሰኙ ቅሬታቸው እንዲታይላቸው ለሚኒስቴሩ ይግባኝ ማለት ይችላሉ፡፡

31.2. ባለሥልጣኑ የወሰነውን ውሳኔ በጽሁፍ እንዲሰጣቸው መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ውሳኔው ለምን፣እንዴት፣መቼ እና በማን እንደተወሰነ ዝርዝር መረጃ ይኖረዋል፡፡

31.3. ውሳኔው በጽሁፍ ከደረሳቸው ቀን ጀምሮ ከባለሥልጣኑ የጽሁፍ ውሳኔ ጋር ቅሬታቸውን በጽሁፍ በመግለጽ እና በማስረጃ አስደግፈው በማያያዝ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ይግባኛቸውን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ በተጠቀሰው ሰላሳ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ያላቀረበ በውሳኔው እንደ ተስማማ ስለሚቆጠር አሳማኝ እና በቂ ምክንያት እስካላቀረበ ድረስ ይግባኝ ማቅረብ አይችልም፡፡

## 32. የሽግግር ወቅት

በሥራ ላይ ያሉ ነገር ግን ከላይ የተመለከተውን መስፈርት የማያሟሉ የሐመር ሰራተኞች፣አምራቾች፣ጠጋኞች እና አስመጪዎች ይህ መመሪያ በወጣ በሁለት አመት ውስጥ በሥልጠና እንዲያሟሉ ይደረጋል፡፡

## 33. መመሪያ ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ ይህ መመሪያ መሻሻል አለበት ብሎ በአመነ ጊዜ መመሪያውን ሊያሻሽለው ይችላል፡፡ የተሻሻሉ የዚህ መመሪያ አንቀጾች ወይም የተጨመሩ አዳዲስ አንቀጾች የዚህ መመሪያ አካል ይሆናሉ፡፡

## 34. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በትራንስፖርት አና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ጸድቆ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡